ቁ=35 OFAG P 02.1/6
ቀን 16/08/2016

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለአቶ አስማረ ይገዙ
የመንግስት ግዥ አገልግሎት
ዋና ዳይሬክተር
<u>አዲስ አበባ</u>

መ/ቤታችን በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት የፋይናንሻልና ህጋዊነት እንዲሁም የክዋኔ ኦዲት የሚያከናውን መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሠረት መ/ቤታችን የመንግስት ግዥ አገልግሎት የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ አፈጻጸም ውጤታማነትን በተመለከተ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የአሠራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን ለይቶ በማውጣት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለመስጠት የክዋኔ ኦዲት መካሄዱ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት ለክዋኔ ኦዲቱ የሚጠቅሙ ማስረጃዎችና መረጃዎች ከአገልግሎት መ/ቤቱ እና ከባለድርሻ አካላት ከተሰበሰቡና ከተተነተኑ በኋላ ኦዲቱ ተጠናቆ የተገኘውን ውጤትና የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የያዘ ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት በደብዳቤ ቁጥር OFAG.P.02.1/5 በቀን 5/7/2016 ዓ.ም መላካችን ይታወሳል፡፡

በመሆኑም በተላከላችሁ ረቂቅ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ ያላችሁን አስተያየት የገለጻችሁና በመውጫ ስብሰባ ወቅትም በኦዲት ግኝቶቹ ላይ የተደረገውን ውይይት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ <u>29</u> ገጽ ሪፖርት እና <u>14</u> ገጽ አባሪ በድምሩ <u>43</u> ገጽ የመጨረሻውን የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን ሲሆን በመ/ቤታችን የማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም መሰረት ሪፖርቱን በዓመታዊ ሪፖርታችን ውስጥ በማካተት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምናቀርብ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

በተጨማሪም በተላከላችሁ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መሠረት በኦዲት ወቅት የተገኙ ዋና ዋና የአሰራር ክፍተቶችንና ድክመቶችን አስመልክቶ የማስተካከያ እርምጃዎችን በመውሰድ አሰራሩ ሕግን የተከተለ፣ ግልጽ እና ውጤታማ ማድረግ ይጠበቅባችኋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

... ብርሀን አታለል
የኢኮኖሚ አገልግሎቶች የክዋኔ ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

በመሆኑም ለክትትል ያመቸን ዘንድ መ/ቤታችሁን በተመለከተ በተደረገው የክዋኔ ኦዲት ወቅት ለተለዩ ክፍተቶች እና የተሰጣችሁን የማሻሻያ አስተያየቶች ተግባራዊ የምታደርጉበትን መርሀ-ግብር ከዚህ ደብዳቤ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት ነድፋችሁ በአስራ አምስት የስራ ቀናት እንድታሳውቁን እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ጳውሎስ ዘሪሁን አታለል
የኢኮኖሚ አገልግሎቶች የክዋኔ ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ

- ለክቡር አቶ አህመድ ሽዴ
  የገንዘብ ሚኒስትር
  <u>አዲስ አበባ</u>

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የመንግስት ግዥ አገልግሎት የተሸከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ አፈጻጸም ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሚያዚያ/2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ........ ii

በኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች /Executive summary/ ........ iv

ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የመንግስት ግዥ አገልግሎት ራዕይና ዕሴቶች፣ ........ 2

የአገልግሎቱ ዓላማ ........ 2

የአገልግሎቱ ሥልጣንና ተግባር ........ 3

የኦዲቱ ዓላማ ........ 3

የኦዲት አካባቢ ........ 4

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 4

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ........ 4

የአገልግሎቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ........ 5

ድርጅታዊ መዋቅር ........ 5

የሰው ኃይል ........ 5

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ........ 5

የፋይናንስ ምንጭ ........ 5

የግዥና የውል አስተዳደር የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process description) ........ 6

ክፍል ሁለት ........ 8

የኦዲቱ ግኝቶች ........ 8

የአገልግሎቱን ስትራቴጂዎችና የአሰራር መመሪያዎች ማዘጋጀቱንና በቦርድ ማጸደቁን በተመለከተ ........ 8

ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የተሰበሰበ መሆኑን በተመለከተ ........ 9

አገልግሎት መ/ቤቱ የሚያከናውናቸውን ግዥዎች በበጀት መደገፉን የሚያረጋግጥ መሆኑን በተመለከተ፡- ..... 10

አገልግሎት መ/ቤቱ ግዥ ሲፈፀም አገልግሎት ጠያቂዎች ግዥውን የሚፈልጉበትን ጊዜ እና መጠን ከግንዛቤ ያስገባ መሆኑን በተመለከተ ........ 11

በአገልግሎቱ የሚከናወኑ ግዥዎችን በግዥ ፍላጎት፣ በናሙናና በስፔሲፊኬሽኑ መሰረት መረከቡን በተመለከተ 14

አገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች በ14 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ .... 16

አገልግሎቱ አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ (liquidity damage) ማስከፈሉን በተመለከተ ........ 17

አገልግሎቱ የተሽከርካሪዎችን ግዥ ሲፈጽም መለዋወጫዎቹ እና የጥገና አገልግሎት ተደራሽነትን ከግምት ውስጥ ማስገባቱን በተመለከተ ........ 18

አገልግሎቱ በኢፌዴሪ የግዥና ንብረት ባለስልጣን እና ከኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት በተገኘው የገበያ ዋጋ ጋር ማነፃፀሩን በተመለከተ ........ 20

አገልግሎቱ የጨረታ ማስታወቂያው ለህዝብ በይፋ ያወጣ መሆኑን በተመለከተ ........ 21

አገልግሎቱ የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እና ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት የዘረጋ መሆኑን በተመለከተ ........ 22

አገልግሎቱ የተገልጋዮችን አቤቱታና ቅሬታ ተቀብሎ መልስ መስጠቱን በተመለከተ ........ 23

ክፍል ሦስት ........ 25

የመደምደሚያ ሀሳቦች ........ 25

ክፍል አራት ........ 27

የማሻሻያ ሀሳቦች ........ 27

አባሪ 1፡ የኢፌዴሪ መንግስት ግዥ አገልግሎት ድርጅታዊ መዋቅር ........ vii

አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) ........ viii

አባሪ 3፡ በናሙና የተመረጡ መስሪያ ቤቶች ስም ዝርዝር ........ xi

# በኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች /Executive summary/

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (ISSAIS) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሲሆን፣ ኦዲቱ በኢፌዴሪ የመንግስት ግዥ አገልግሎት የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ አፈጻጸም ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ ነው፡፡ ክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2012 እስከ 2016 2ኛ ሩብ ዓመት የተከናወኑ ተግባራቶችን በማካተት ነው፡፡ የኦዲቱም ዓላማ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የኢፌዴሪ መንግስት ግዥ አገልግሎት በተሽከርካሪ እና መለዋወጫ ግዥ ላይ ያካሄዳቸውን የግዥ ሂደቶች አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም ሲሆን በተለይ ኦዲቱ አገልግሎት ጠያቂ መ/ቤቶች የሚፈልጓቸውን ተሽከርካሪዎችና መለዋወጫዎች በኮንትራት ውሉ እና በስፔስፊኬሽኑ መሰረት መረከባቸውን፣ እንዲሁም መንግስት ከጥቅል ግዥ የሚያገኘውን ጥቅም ውጤታማ መሆኑን በመገምገም በአሰራር ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ከነበሩ በመለየት ችግሮቹ የሚቀረፉበትን ወይም የሚሻሻሉበትን የማሻሻያ ሀሣቦች ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

ኦዲቱ በኢፌዴሪ መንግስት ግዥ አገልግሎት የተሽከርርካሪ እና መለዋወጫ ግዥ ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ ሲሆን በዚሁ መሰረት በኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ የአገልግሎት መስሪያ ቤቱ የውስጥ አሰራር መመሪያ እንዲሻሻል በተደጋጋሚ ለቦርዱ የቀረበ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ያልጸደቀ መሆኑ፣ በአገልግሎቱ በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችን (የተሽከረካሪ ጎማን ጨምሮ) የግዥ ፍላጎት ሳያቀርቡ ግዥ የሚፈጽሙ መስሪያ ቤቶች በመኖራቸው በእነርሱ ላይ በአስተዳደራዊ እርምጃ ተጠያቂ የሚሆኑበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ፡፡
- አገልግሎቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ወይም በአመት 12 ጊዜ መሰብሰብ ሲገባው በ2012 በጀት ዓመት 4ጊዜ፣በ2013 በጀት ዓመት 8ጊዜ በ2014 ሦስት ጊዜ እና በ2015 በጀት አመት ሦስት ጊዜ ብቻ የተሰበሰበ መሆኑ፣

- አገልግሎቱ አገልግሎት በሚሰጣቸው ባለ በጀት መ/ቤቶች በማዕቀፍ ለሚገዙ ተሽከርካሪዎችና መለዋወጫዎች (የተሽከርካሪ ጎማን ጨምሮ) በበጀት መደገፋቸውን እና አለመደገፋቸውን የማያረጋግጥ (ዕውቅና የሌለው) መሆኑ፣
- አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫ ጎማዎችን አገልግሎት ፈላጊዎቹ በሚፈልጉበት ጊዜ እና መጠን የማያቀርብ/ አሸናፊዎቹ የማያቀርቡ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ አገልግሎት በሚሰጣቸው መ/ቤቶች የሚፈልጓቸውን የተሽከርካሪ ጎማዎች በማዕቀፍ ግዥ ውስጥ ያላካተተ መሆኑ (ጨረታ ላይ የወጣው የጎማ ዓይነት አገልግሎት ከሚሰጣቸው መ/ቤቶች ፍላጎት ጋር ያልተጣጣመ መሆኑ)፣
- አገልግሎቱ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪ፤ ጎማዎችን እና መለዋወጫዎችን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ (liquidity damage) የማይቀጣ መሆኑን፣
- በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪ ግዥን በተመለከተ የባትሪ መሙያ ጣቢያዎች (Charging centers)፣ ከጥገና አገልግሎት፣ መለዋወጫና ኢንሹራንስ ጋር በተያያዘ የአዋጭነት ጥናት ያልተጠና መሆኑ፤
- አገልግሎቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የግዥና ንብረት ባለስልጣን እና ከኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የገበያ መረጃ በየጊዜው በመሰብሰብ በማደራጀትና አቅራቢዎች ከሰጡት ዋጋ ጋር በማነጻጸር ለግዥ ሂደቱ በግብዓትነት የማይጠቀም መሆኑ፣

የሚሉት ናቸው፡፡ በመሆኑም፡-

- አገልግሎቱ የሚጠቀምባቸውን የአሰራር መመሪያዎች አሁን እየተሻሻለ በሚገኘው የግዥ አዋጅ መሰረት እንዲጣጣሙ በማድረግ መክለስ በቦርዱ ማጸደቅ ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም በሥራ ላይ ባለው የግዥ መመሪያ ያልተሸፈኑ የጉዳት ካሣ ክፍያ አከፋፈል፣ ዕቃዎችን በማዕቀፍ ለመግዛት አስፈላጊ የሆነው አነስተኛ ብዛት የመሳሰሉት እንዲካተቱ ለሚንስቴር መ/ቤቱ በማሳወቅና ግብዓት በመስጠት እንዲካተቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- አገልግሎቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ በህግ በተቀመጠው መሰረት በየወሩ በመሰብሰብ የአገልግሎቱን አፈጻጸም መገምገምና የሚቀርቡለትን የተለያዩ መመሪያዎች መርምሮ ሊያጸድቅ ይገባል፡፡

- አገልግሎቱ ለሚፈጽማቸው የተሽከርካሪ ግዥዎች የግዥ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ለግዥዎቹ በቂ በጀት መያዙን ማረጋገጥ፤ በማዕቀፍ ለሚገዙ ግዥዎች ደግሞ ግዥውን ከጠየቀው መስሪያ ቤት ጋር በመቀናጀት በበጀት መደገፋቸውን በማረጋገጥ የግዥ ሂደቱ በሚፈለግበት ጊዜና መጠን እና በተያዘው በጀት በመፈጸም የቀረበው ዋጋ ደግሞ ከተያዘው በጀት በላይ ከሆነ ግዥን ከጠየቀው አካል ጋር በመመካከር በመወሰን የተቋቋመበትን አላማ ሊያሳካ ይገባል፡፡
- አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ ሲፈጽም ሁሉም የመንግስት ተቋማት የጠየቁትን ግዥ መሰረት ያደረገ ዝርዝር ስፔስፊኬሽን ባለሙያ በማዘጋጀት ጨረታ ሊያወጣና ውድድሩን አሸንፈው እንዲያቀርቡ ከተመረጡት ጋር ውል የገባባቸውን ንብረቶች በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸው የሥራ ዝርዝር /Specification/ እና ናሙና መሰረት መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ለተግባራዊነቱም ክትትል የሚያደርግበት፣ እንዲሁም በማዕቀፍ የሚገዙ መለዋወጫዎችንና ጎማዎች አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መ/ቤቶች የግዥ ማዘዣ (perchese order) ሲደርሳቸው በሥራ ዝርዝር /Specification/ እና ናሙና መሰረት በ14 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን የሚረጋግጥበት የክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- አገልግሎቱ ውድድሩን አሸንፈው አሸናፊ የተደረጉና ውል የገቡ አቅራቢዎች በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎችን በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ (liquidity damage) የሚቀጡበትን አግባብ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከገንዘብ ሚኒስቴር እና የመንግስት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን ጋር በመመካከር ውል በገባው በአገልግሎቱና ክፍያ በሚፈጽሙ ባለበጀት መ/ቤቶች የተፈጠረውን የትግበራ የህግ ክፍተት ሊስተካከል እና የሚቀጡበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡
- አገልግሎቱ የተሽከርካሪዎችን ግዥ ሲፈጽም ዋጋቸው እና አገልግሎታቸው ተመጣጣኝ እንዲሆን ከሃገሪቱ ነባራዊ እና የአየር ሁኔታ የተጣጣሙ እንዲሆኑ፤ የመለዋወጫ አቅርቦት በሃገር ውስጥ መኖሩንና የጥገና አገልግሎትን ተደራሽነት ግምት እንዲሁም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ሲሆኑ ደግሞ ባትሪያቸውን የሚሞሉበት ጣቢያዎች (Charging centers)

መኖራቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት በጥናት ተመርኩዞ መግዛት ይኖርበታል፡፡

- አገልግሎቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የግዥና ንብረት ባለስልጣን እና ከኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የተገኘው የገበያ መረጃ በየጊዜው በመሰብሰብ በማደራጀትና አቅራቢዎች ከሰጡት ዋጋ ጋር በማነጻጸር ለግዥ ሂደቱ በግብዓትነት ሊጠቀም ይገባል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. መንግስት በየዓመቱ ከሚመድበው በጀት ውስጥ ከ65 እስከ 70 በመቶ የሚደርሰው ለግዥ የሚውል ነው፡፡ የግዥ አፈጻጸም ውጤታማነት የሚለካው ፍላጎትን ለማሟላት ወጭ ለተደረገ ገንዘብ ተገቢውን ጥቅም ማስገኘት መቻሉ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከፍተኛ መጠን ያለው የመንግስት ሃብት የሚፈስበት የመንግስት ግዥ ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘቱ አፈፃጸሙ አዝጋሚና ለብክነት የተጋለጠ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለግዥ ስራ የሚመደቡ ባለሙያዎችም በቂ የትምህርት ዝግጅት የሌላቸውና በልምድ ብቻ የሚሰሩ የነበሩ በመሆናቸው እና ንብረት ማስወገድንም በተመለከተ ጥቅም ላይ የማይውል የመንግስት ንብረት በተገቢው ጊዜ የማስወገድ ባህል በአገራችን የተለመደ አልነበረም፡፡ በዚሁ ምክንያት በመንግስት መስሪያ ቤቶች ይዞታ ስር የሚገኙ ንብረቶች ለአገልግሎት በማይፈለጉበት ጊዜ በወቅቱ ስለማይወገዱ ለዝናብና ፀሀይ ተጋልጠው በሚደርስባቸው እንግልት ዋጋቸው እየቀነሰ መንግስት ከንብረቶቹ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም የሚያጣ ከመሆኑም በላይ ለሌላ አገልግሎት ሊውል የሚገባውን ቦታ ጨምሮ በመያዝ ከፍተኛ ችግር አስከትሏል፡፡
2. ስለሆነም ለመንግስት ግዥ ለተከፈለ ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም መገኘቱን ለማረጋገጥ የግዥ አፈጻጸም እና የንብረት አስተዳደር ስርዓቱን የበለጠ ሃብትና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሁም ግልጽ አሰራርን መሰረት አድርጎ በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሚያስችሉ አደረጃጀቶች እንዲኖሩት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
3. በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ረገድ በተደረገው መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት የመንግስት ግዥ አፈጻጸምን ብቃት በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻል ይጠቅማሉ ተብለው የታመነባቸው የጥናቱ ሃሳቦች የህግ መሰረት እንዲኖራቸው ለማድረግ ተሻሽሎ በወጣው የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ከተካተቱ ለውጦች መካከል አንደኛው በመንግስት መስሪያ ቤቶች በወል የሚፈለጉ እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን እቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በአንድ ማዕከላዊ ተቋም አማካኝነት አጠቃሎ መግዛት ጠቃሚ መሆኑ ተደንግጓል፡፡
4. በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን ስራዎች እና የንብረት ማስወገድን ጨምሮ በሃላፊነት የሚመራ እራሱን የቻለ አካል ማደራጀት ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት የመንግስት ግዥ

አገልግሎት የሚባል ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣ ደንብ ቁጥር 184/2002 መሰረት ተጠሪነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር በመሆን እንዲቋቋም ተደርጓል:: በመጨረሻም በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 ተጠሪነቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር እንዲሆን ተደርጓል::

## የመንግስት ግዥ አገልግሎት ራዕይና ዕሴቶች፣

### ራዕይ

5. የአገልግሎቱ ራዕይ "በአገሪቱ የላቀና ተመራጭ የግዥና የንብረት ማስወገድ አገልግሎት እንዲሁም በዘርፉ የምክርና ስልጠና አገልግሎት ሰጭ ተቋም መሆን፣" የሚል ነው::

### ዕሴቶች

- ተገልጋይ ተኮር /Customer focus/
- የእኔነት ስሜት /sense of ownership/
- ግልጽነት /Transparency/
- ታማኝነት /Honesty/
- ተጠያቂነት /Accountability/
- ሚስጥር ጠባቂነት /confidentiality/
- በቡድን መስራት /team work/
- ተነሳሽነት /motivation/

## የአገልግሎቱ ዓላማ

6. አገልግሎቱ የሚከተሉት አላማዎች አሉት::
   1) የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ እቃና አገልግሎቶች እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸው እቃዎችና አገልግሎቶች ከከፍተኛ ግዥ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኝ ተመጣጣኝ ዋጋ ፣ በተገቢው ጊዜና በተፈላጊው ጥራት እንዲቀርቡ ማስቻል::
   2) በሽያጭ እንዲወገዱ ውሳኔ የተሰጠባቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ንብረቶች በተቀላጠፈ አኳኋን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲወገዱ ማስቻል እና
   3) ለመንግስት የልማት ድርጅቶች በእቃና አገልግሎት ግዥ እንዲሁም በንብረት ማስወገድ ረገድ እገዛ ማድረግ የሚሉት ናቸው::

## የአገልግሎቱ ሥልጣንና ተግባር

7. አገልግሎቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው ደንብ ቁጥር 184/2002 የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ተሰጥቷል፡፡

ሀ/ ዝርዝራቸው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መመሪያ የሚወሰን የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ እቃዎችና አገልግሎቶች እንዲሁም አገራዊ እስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን እቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ያከናውናል፡፡

ለ/ ግምታቸው በሚኒስቴሩ መመሪያ ከሚወሰን የገንዘብ መጠን በላይ የሆነ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ሃላፊነት ስር ያሉ በሽያጭ እንዲወገዱ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ንብረቶች ይሸጣል፡፡

ሐ/ ለመንግስት መስሪያ ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ፣ ለክልል መንግስታት እና ለግሉ ዘርፍ ፤

1) በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የአገር ውስጥና የአለም አቀፍ የግዥ አገልግሎት ይሰጣል፣

2) የግዥ አፈጻጸምን የሚመለከት የምክርና ስልጠና አገልግሎት ይሰጣል፡፡

መ/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ዋጋ ያስከፍላል፡፡

ሠ/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ይከሰሳል፣

ረ/ ዓላማውን ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን ያከናውናል፣

የሚሉት ናቸው፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

8. የኦዲቱ ዓላማ በኢፌዴሪ የመንግስት ግዥ አገልግሎት የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ አፈጻጸም ውጤታማነትን በተመለከተ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ የተከናወነ መሆኑን መገምገምና አፈጻጸሙ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ አጥጋቢ ሆኖ ያልተገኘባቸውን ምክንያቶች በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ

9. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) "የመንግስት ግዥ አገልግሎት የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ አፈጻጸም ውጤታማነትን በተመለከተ" የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

10. ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ ሁለት የትኩረት አቅጣጫዎች የተለዩ ሲሆን እነርሱም፡-
   1. አገልግሎቱ የሚያከናውናቸው የተሽከርካሪና የተሽከርካሪ መለዋወጫ ግዥዎች በግዥ ደንብና መመሪያ እንዲሁም በኮንትራት ውሎች መሰረት የሚገዛበት፣ የሚረከብበት እና የሚያከፋፍልበትን የአሰራር ስርዓት መገምገም፣
   2. አገልግሎቱ የተሽከርካሪና መለዋወጫ ግዥን በብቃት ለመወጣት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

11. ለኦዲቱ የተመረጡትን ሁለት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 20 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች(Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ ከግዥና ውል አስተዳደር የውስጥ አሰራር መመሪያ፣ የመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001፣ General condition of the contract ፣ከመንግስት ግዥ አገልግሎት መቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 184/2002 ፣ የግዥ መመሪያ እንዲሁም ከመልካም ተሞክሮ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የተዘጋጁት ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች ቀርበው አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ መመዘኛ መስፈርቱ ከዚህ ሪፖርት ጋር (በአባሪ 2) ተያይዟል፡

## የአገልግሎቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

12. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት ግዥ አገልግሎት ተጠሪነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሆኖ በቦርድ የሚመራ ሲሆን በስሩ አንድ ዋና ዳይሬክተር፣ ሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ አንድ የዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት፣ አንድ የስራ አመራር ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ አራት መሪ ሥራ አስፈጻሚዎች እና 12 ዳይሬክተሮች አሉት፡፡ (ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ 1 ተያይዟል)

### የሰው ኃይል

13. የኢፌዴሪ ግዥ አገልግሎት ለኦዲት ቡድኑ ባቀረበው ማስረጃ ለማወቅ እንደተቻለው በአጠቃላይ በመዋቅሩ 247 ስራተኞች የሚያስፈልጉት ቢሆንም በስራ ላይ ያሉ ሰራተኞች 155 ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | የትምህርት ደረጃ | ብዛት | ወንድ | ሴት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ማስተርስ | 18 | 12 | 6 |
| 2 | ቢኤ | 82 | 22 | 60 |
| 3 | ኤልኤልቢ | 2 | --- | 2 |
| 4 | ዲፕሎማ | 12 | 4 | 8 |
| 5 | ሌሎች | 41 | 17 | 24 |
| | **ድምር** | 155 | 55 | 100 |

### የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

14. ኦዲቱ የተከናወነው በኢፌዴሪ መንግስት ግዥ አገልግሎት ሲሆን ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2012 እስከ 2016 2ኛ ሩብ ዓመት ድረስ ያለውን ጊዜ ነው፡፡ ኦዲቱ ተያያዥ የሆኑና አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች/መረጃዎች መመርመር /Document Review/፣ በአካል በመገኘት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች መጠይቅ /Interviews/ በማቅረብ፣ መረጃዎችን በመተንተን፣ በመመርመርና በማገናዘብ የተከናወነ ነው፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

15. የኢፌዴሪ ግዥ አገልግሎት ስራውን የሚያከናውነው በመንግስት በሚመደብለት በጀት ሲሆን በ2012፣ በ2013፣ በ2014፣ በ2015 እና በ2016 በጀት ዓመት እንደየቅደም

ተከተሉ ከመንግስት የተመደበለት መደበኛ በጀት እና አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| የበጀት ዓ.ም | የበጀት ዓይነት | የፀደቀና የተስተካከለ በጀት (ብር) | ሥራ ላይ የዋለ (ብር) | አፈፃፀም በመቶኛ % |
|---|---|---|---|---|
| 2012 | መደበኛ | 24,746,430.00 | 74,354,076.00 | 300% |
| 2013 | መደበኛ | 32,785,000.00 | 27,654,970.45 | 84% |
| 2014 | መደበኛ | 41,292,115.39 | 34,209,753.49 | 83% |
| 2015 | መደበኛ | 38,604,617.00 | 26,975,361.90 | 70% |
| 2016 2ኛ ሩብ አመት | | 41,841,686.00 | 18,185,207.97 | 42% |

**የግዥና የውል አስተዳደር የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process description)**

16. በፌዴራል የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች (common user items) እንዲሁም ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ከክልል ወይም ከተማ አስተዳደሮች እና ከግሉ ዘርፍ የሚቀርብለትን የግዥ አገልግሎት የፍላጎት ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ ተፈላጊ መረጃዎችን በዓይነትና በመጠን ለይቶ ያደራጃል፣ የግዥ ዓይነቶችን ለይቶ የግዥ ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡ ለእያንዳንዱ ግዥ ስፔስፊኬሽን ወይም ቢጋር (terms of reference) ያካተተ የተሟላ የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት በግዥ እቅዱ መሰረት ለየግዥው ዓይነት የጨረታ ማስታወቂያ ያወጣል፡፡

17. የጨረታ አጽዳቂ ኮሚቴ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ የቴክኒክ እና የፋይናንስ የግምገማ ውጤት ያፀድቃል፡፡ ከብር 100,000,000 በላይ (በስራ አመራር ቦርዱ) የሚያጸድቅ ሲሆን ከዚህ የገንዘብ መጠን በታች የሆነው በግዥ አጸዳቂ ኮሚቴ ይጸድቃል፡፡ አሸናፊውን ተወዳዳሪ /ተጫራችን/ በመለየት ውጤቱን ለሚመለከታቸው ጨረታ የሚፈጸም ግዥ(international competitive bid) ከሆነ እንደአስፈላጊነቱ ሌተር ኦፍ ክሬዲት(LC) በመክፈት፣ የትራንዚትና ክሊሪንግ ስራዎችን ተከታትሎ ያሳውቃል፡፡ እንዲሁም የማዕቀፍ ውል ይገባል አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ በአለም አቀፍ ያስፈፅማል፡፡ ይህ የስራ ሂደት ከላይ ከተገለጹት ተግባራት በተጨማሪ የተሸናፊና አሸናፊ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ(Bid Bond) እንዲመለስ የማድረግ፣ የጨረታ ማስከበሪያ ጊዜውን እየጠበቀ የማራዘሚያ ደብዳቤ የማዘጋጀት፣ የውል ማስከበሪያ(Performance Bond) የመቀበል፣ የመያዝና የማስተዳደር እንዲሁም

የተገዙት ዕቃዎች / አገልግሎቶች በውሉ መሰረት ለተጠቃሚዎች መድረሳቸውን በማረጋገጥ የውል አስተዳደር ስራዎችን ያከናውናል፡:

## ክፍል ሁለት

## የኦዲቱ ግኝቶች

**የአገልግሎቱን ስትራቴጂዎችና የአሰራር መመሪያዎች ማዘጋጀቱንና በቦርድ ማጸደቁን በተመለከተ**

18. ስትራቴጂዎችና የአሰራር መመሪያዎች በማዘጋጀት በበላይነት ለሚያስተዳድረው ቦርድ በማቅረብ ሊያጸድቅና ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

19. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ✓ ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ የአገልግሎት መስሪያ ቤቱ የውስጥ አሰራር መመሪያ እንዲሻሻል በተደጋጋሚ ለቦርዱ የቀረበ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ያልጸደቀ መሆኑ፤
- ✓ በአገልግሎቱ በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችን (የተሽከረካሪ ጎማን ጨምሮ) የግዥ ፍላጎት ሳያቀርቡ ግዥ የሚፈጽሙ መስሪያ ቤቶች በመኖራቸው በእነርሱ ላይ በአስተዳደራዊ እርምጃ ተጠያቂ የሚሆኑበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡(የግዥ ፍላጎት እንዲያቀርቡ 2 ጊዜ ተጠይቀው ሳያቀርቡ ለ3ኛ ጊዜ እንዲያቀርቡ የተጠየቀበት የመስሪያ ቤቶች ስም ዝርዝር በአባሪ 4 ተያይዟል፡፡)

20. የአገልግሎት መስሪያ ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው ለነባራዊ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ በቀረቡት የውስጥ አሰራር መመሪያዎች ላይ በየጊዜው በበላይ አመራሩ የተለያዩ ግብዓቶች እየተሰጠና እየተስተካከለ የቆዩ ሲሆን በመጽደቅ ሂደት ካለው አዲሱ የግዥ አዋጅ ማሻሻያ ጋርም መጣጣም ስለሚገባው አዋጁ እንደጸደቀ ሁሉንም መመሪያዎች ለስራ አመራሩ ቦርድ በዚህ በጀት ዓመት ውስጥ በማቅረብና በማጸደቅ ለማጠናቀቅ በተከለሰው እቅዳችን ውስጥ ተካቷል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

21. የግዥ መመሪያው በየጊዜው የሚደረሱ መለዋወጦችን ባገናዘበ መልኩ በየወቅቱ ባለመሻሻሉ ለግዥ ስርዓቱ እንቅፋት በመሆን አገልግሎት ጠያቂ መ/ቤቶች ባቀዱት የስራ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የተሰበሰበ መሆኑን በተመለከተ

22. አገልግሎቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ በደንብ ቁጥር 184/2002 መሰረት ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ሊሰበሰብና የአገልግሎቱን አፈጻጸም ሊገመግምና ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል::

23. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች አገልግሎቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ወይም በዓመት 12 ጊዜ መሰብሰብ ሲገባው በ2012 በጀት ዓመት 4ጊዜ፣በ2013 በጀት ዓመት 8ጊዜ በ2014 በጀት ዓመት ሦስት ጊዜ እና በ2015 በጀት ዓመት ሦስት ጊዜ ብቻ የተሰበሰቡ መሆኑ እና በዚህም ስብሰባ ሁሉም ተሰብሳቢዎች ቃለ-ጉባኤው ላይ ያልፈረሙ መሆኑን ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

24. የአገልግሎት መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ በሰጡት መልስ ቦርዱ ቢያንስ በወር 1ጊዜ ያልተሰበሰበበት ምክንያት የተቋሙ ዋና ስራ የሆነው የግዥ ስራ ከውጭ ምንዛሬ እጥረት ጋር በተያያዘ የተዳከመ በመሆኑ የተነሳ በየወሩ ለመሰብሰብ ለስብሰባው በቂ አጀንዳ ባለመኖሩ ምክንያት የተፈጠረ መሆኑን ጠቅሰው የስራ አመራር ቦርድ ቃለ-ጉባዔ የሚጸድቀው ደግሞ በቀጣይ ስብሰባ ላይ በአጀንዳነት ተይዞ ሲሆን ቃለ-ጉባኤው ከመጽደቁ በፊት አንዳንድ የቦርድ አባላት በሌላ መንግስታዊ ተልዕኮ ተቋም ሲቀይሩ ከቦርድ አባልነት ስለሚወጡ የቦርድ አባሉን አግኝተው በቃለ-ጉባኤው ላይ ለማስፈረም እየተቸገሩ መሆኑ እና በቀጣይ ግን በተቻለ መጠን አሰራሩን በመቀየር ሁሉም የቦርድ አባላት እንዲፈርሙ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

25. የአገልግሎት መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ይህን ይበሉ እንጂ በአገልግሎቱ መቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 184/2004 ቁጥር 10 ንዑስ ቁጥር 1 ቦርዱ ቢያንስ በወር 1 ጊዜ መሰብሰብ እንዳለበት በግልጽ ስለተቀመጠ እና ቢያንስ አንድ ጊዜ በተሰበሰቡት ስብሰባ ላይ በአጀንዳ የመወያያ አጀንዳ (የመወያያ ነጥብ) አለመኖሩን የተጠቀሰ ነጥብ ባለመኖሩ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

26. ቦርዱ በአቅዱ እና በደንቡ መሰረት በየወሩ ባለመሰብሰቡ የተሸከርካሪና የመለዋወጫ ግዥዎች እንዳይገመገም እና አቅጣጫ መስጠትን አዘግይቷል፡፡

**አገልግሎት መ/ቤቱ የሚያከናውናቸውን ግዥዎች በበጀት መደገፉን የሚያረጋግጥ መሆኑን በተመለከተ፡-**

27. አገልግሎቱ የግዥ አገልግሎት ጠያቂ መ/ቤቶች ግዥ በሚጠይቁበት ጊዜ በበጀት መደገፉን ሊያረጋግጥ ይገባል፣

28. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ✓ አገልግሎቱ ለሁሉም የተሽከርካሪ ግዥ አፈጻጸም ገንዘብ ሚኒስቴር የግዥ ትዕዛዝ ሲያዝዘው ግዥውን መፈጸም እንጂ ግዥው በበጀት ይደገፍ አይደገፍ እውቅናው የሌለው መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎቱ አገልግሎት በሚሰጣቸው መ/ቤቶች በማዕቀፍ ለሚገዛቸው ተሽከርካሪዎችና መለዋወጫ ዕቃዎች (የተሽከርካሪ ጎማን ጨምሮ) በበጀት መደገፋቸውን እና አለመደገፋቸውን የማያረጋግጥ (ዕውቅና የሌለው) መሆኑ፣

29. ጉዳዩን በሚመለከት ለሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በማዕቀፍ ለሚገዙ ግዥዎች (የተሽከርካሪ ጎማን ጨምሮ) ክፍያውን እራሳቸው አገልግሎት ጠያቂ መ/ቤቶች ስለሚፈጽሙ አገልግሎቱ እውቅና የሌለው መሆኑ፤ በስትራቴጂክ ግዥዎች (ተሽከርካሪዎችን ጨምሮ) ገንዘብ ሚኒስቴር ግዛ ሲለው (የግዥ ትዕዛዝ ሲያዝዘው) መግዛት እንጂ አገልግሎቱ ስለሚገዛው ዕቃ ለማን እንደሚገዛ እና በጀት ስለመኖሩ እውቅና የሌለው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

30. ለአገልግሎቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ የመኪና ግዥን በተመለከተ በጀት የሚጸድቀውና የሚቆጣጠረው የገንዘብ ሚ/ር ስለሆነ ግዥ በበጀት መደገፉን መጠየቅ አስፈላጊ መስሎ እንደማይታያቸው እና በማዕቀፍ ለሚፈጸሙ ግዥዎች ደግሞ መ/ቤቶች በተፈቀደላቸው በጀት መሰረት የፍላጎት መግለጫ እንዲያቀርቡ ከማድረግ ውጭ የተፈቀደላቸው በጀት መጣጣሙን እንደማያረጋግጡ ነገር ግን አሁን በተዘረጋው የመንግስት የኤሌክትሮኒክ የግዥ ዘዴ (ኢጂፒ) የግዥ ትዕዛዝ ከተመደበው በጀት መጣጣሙን አረጋግጠው እንዲተገበሩ የሚያስገድድ በመሆኑ ለወደፊት ችግሩን እንደሚቀርፉ፣ በጀት ማወቅ የሚችሉበት ዕድል ቢኖር በጣም ፍላጎታቸው እንደሆነ እና በኢጂፒ ሲስተም እንደሚደገፉ ገልጸዋል፡፡

31. በግዥ መመሪያው መሰረት ማንኛውም የግዥ ዕቅድ ሲዘጋጅ መጀመሪያ በበጀት መደገፉ መረጋገጥ ስላለበት ተቋማት በጀት ሳያሲዙ የግዥ ጥያቄ የሚያቀርቡ ከሆነ

አገልግሎቱ ጨረታ አውጥቶ የግዥ ሂደቱን ከፈጸመና አሸናፊውን ካሳወቀ በኋላ ተቋማት በጀት ስለሌላቸው ግዥውን ሳያከናውኑ እንዲቀር ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አገልግሎት መ/ቤቱ ግዥ ሲፈፅም አገልግሎት ጠያቂዎች ግዥውን የሚፈልጉበትን ጊዜ እና መጠን ከግንዛቤ ያስገባ መሆኑን በተመለከተ**

32. አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎችን ግዥ ሂደት ሲፈጽም አገልግሎት ጠያቂዎች ያላቸውን በጀት፣ የሚፈልጉበትን ጊዜ እና መጠን ከግንዛቤ ሊያስገባ ይገባል፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ✓ አገልግሎቱ በ2012 በጀት ዓመት ለፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች 10 ዓይነት የተሽከርካሪ ጎማ በማዕቀፍ ለመግዛት አቅዶ ግዥውን ለመፈጸም ለ3ኛ ጊዜ ጨረታ ያወጣ ቢሆንም በቴክኒክና በናሙና ግምገማ ያለፈ ተጫራች ባለመኖሩ ግዥው ሙሉ በሙሉ ያልተሳካ መሆኑ፤
- ✓ በ2012 በጀት ዓመት ለገቢዎች ሚኒስቴር የ37 ሞተር ሳይክል፣ ለብሄራዊ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን 60 ሞተር ሳይክል፣ ለትምህርት ሚኒስቴር 2ሞተር ሳይክል እና ለኢትዮጵያ ብዝሃህይወት ኢንስቲትዩት 3ሞተር ሳይክል በድምሩ 102 ሞተር ሳይክል ግዥ ተጫራቾች የቅድመ ግምገማ ባለማለፋቸው ግዥው ውድቅ መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎቱ በ2013 በጀት ዓመት በጨረታ ሰነድ ቁጥር PPDS/MOF/ICB/PG//147/12 የተሽከርካሪ ግዥ ለመፈጸም ጨረታ የወጣ ቢሆንም በ2 ሎት ላይ አሸናፊ የሆኑ ሁለት የአገር ውስጥ ተሽከርካሪ ገጣጣሚዎች ውል እንዲፈርሙ የአሸናፊነት ደብዳቤ የተሰጣቸው ቢሆንም በማቅረቢያ ጊዜ ምክንያት ውል ባለመፈረማቸው ግዥው የተሰረዘ መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎቱ በ2013 በጀት ዓመት በጨረታ ሰነድ ቁጥር PPPDS/MOA/ICB/PG/150/12/20 ለግብርና ሚኒስቴር የተሽከርካሪ እና የሞተር ሳይክል ግዥ ለመፈጸም ጨረታ የወጣ ቢሆንም በቴክኒክ ግምገማ ያለፈ ተጫራች ባለመኖሩ፣ የሞተር ሳይክል ግዥ ደግሞ የገበያ ዋጋ ጥናት ባለመገኘቱ ግዥው የተሰረዘ መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎቱ በ2014 በጀት ዓመት በጨረታ ቁጥር PPS/FA2014-2016/ICB/PG/171/ 03/2014 (LOT3) ለፌደራል ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ከ2014-16

ከሚያገለግሉ የማዕቀፍ ስምምነት እቃዎች ውስጥ የተሽከርካሪ ጎማዎች ግዥ አቅዶ ተጫራች ባለመኖሩ ያልተሳካ መሆኑ፤

- ✓ አገልግሎቱ በ2014 በጀት ዓመት ለኢትዮጵያ የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የ3 አውቶሞቢል ተሽከርካሪ ለመግዛት አቅዶ ተጫራች ባለመኖሩ የተሰረዘ መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎቱ በ2014 በጀት ዓመት ለወልዲያ ዩኒቨርስቲ የውሃ ማመላለሻ ቦቴ ለመግዛት አቅዶ ተጫራች ባለመኖሩ ግዥው የተሰረዘ መሆኑ፤
- ✓ በ2014 በጀት ዓመት ለፌደራል ባለበጀት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት የሚውል በቁጥር 39 የሚሆኑ የተሽከርካሪ ጎማዎች ግዥ በወጣው ጨረታ ለ22 ዓይነት ጎማዎች ተጫራች ባለመቅረቡ፣ ለ6ዓይነት ጎማዎች በቴክኒክ ግምገማ ያለፈ ተጫራች ባለመኖሩ፣ ለፋይናንስ ውድድር ያለፈ 1ተጫራች ደግሞ ለ9 ጎማዎች ያቀረበው ዋጋ ከገበያ በላይ በመሆኑ እና ለ2 ጎማዎች የገበያ ዋጋ ባለመገኘቱ የግዥ ሂደቱ ሙሉ በሙሉ የተሰረዘ መሆኑ፤
- ✓ ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ አገልግሎቱ የተሽከርካሪ ጎማዎችን ለማቅረብ ከሁለት አቅራቢዎች ጋር ማለትም ማክ እና ጥላሁን ጫላ ከተባሉ አቅራቢዎች ጋር ውል የተዋዋለ እና ለአምቦ ዩኒቨርስቲ 7 የጎማ አይነቶችን ለማቅረብ ከአቅራቢዎች ጋር በመስማማት ለማቅረብ ዝግጁ ነኝ ሲል በቀን ነሐሴ 6/2013 ዓ.ም ቢያሳውቅም እስከ ነሐሴ 1/2016 ዓ.ም ድረስ ምንም ዓይነት የተሽከርካሪ ጎማ ግዥ ለማንም ባለበጀት መስሪያቤት ያልፈጸመ መሆኑ እና አቅራቢ ድርጅቶች የጉዳት ካሳ ክፍያ(liquidity damage)ያልከፈሉ መሆኑ፤
- ✓ አቅራቢ ድርጅቶች በሚሰጣቸው የግዥ ትዕዛዝ መሰረት ተሽከርካሪዎችን እና መለዋወጫዎችን ማቅረብ ሳይችሉ የሚቀሩ መሆኑ

ታውቋል፡፡

34. ጉዳዩን በተመለከተ ለሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የስራ ኃላፊዎች በተደረገ ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ተወዳዳሪዎች በቴክኒክ ግምገማ ባለማለፋቸው፤ተቋማት የሚፈልጉት ጎማ ጨረታ ላይ ባለመውጣቱ፤ ባላቸው እውቀት ቁጥሩን አጥንተው እንደሚያወጡና ነገር ግን ተቋማት የሚፈልጉት ቁጥር ሊኖር እንደማይችል እንዲሁም ተጠቃሚው እና የጨረታው ባለቤት የስፔስፊኬሽን አለመሟላት ለግዥው መዘግየት ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡

35. የአገልግሎቱ የበላይ ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ የተካተቱት ግድፈቶች መኖራቸውን ገልጸው የተሽከርካሪ ትዕዛዝ የሚሰጠው የተሽከርካሪ ስፔስፊኬሽን እና በጀት የሚመድበው የገንዘብ ሚኒስቴር መሆኑን፤ የተሽከርካሪ መለዋወጫን በተመለከተ ደግሞ አገልግሎቱ በየበጀት ዓመቱ ለሚፈጽመው ጨረታ ከአገልግሎት ጠያቂዎች በሰበሰበው ፍላጎትና ስፔስፊኬሽን መሰረት ሆኖ ከአቅራቢዎች/ከአሸናፊ ድርጅቶች/ ውል ከታሰረ በኋላ በየሩብ ዓመቱ የሚፈልጉትን የጎማ መጠን ከተመደበው አቅራቢ እንዲያሳውቁ በደብዳቤ የሚያሳውቁ መሆኑን እንዲሁም አብዛኛውን ጨረታዎች ያልተሳኩት ተጫራቾች በትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚ/ር የወጣውን ስፔስፊኬሽን ባለማሟላታቸው እንዲሁም የገበያ ዋጋ ባለመገኘቱ መሆኑና የተሰረዘበት ምክንያት ትክክል ካልሆነ የሚሰጡት ምላሽ እንደሌላቸው፤ የዕቅድ ንጽጽር ለቀረበው ደግሞ ተሽከርካሪ ቋሚ እቃ በመሆኑና በየአመቱ ግዥ ስለማይፈጸም አንዱን ዓመት ከሌላው በጀት ዓመት አነጻጽሮ ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ነው ለማለት እንደማይቻል፤ጥላሁን ጫላ እና ማክ ኢንተርናሽናል የተሽከርካሪ ጎማ በወቅቱ አለማቅረባቸውን በተመለከተ ደግሞ፦ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ሁለቱ የሃገር ውስጥ የጎማ አቅራቢዎች የገቡትን ውል ባለመፈጸማቸው የጉዳት ካሳ (liquidity damge) ከቅጣትም አልፎ ያስያዙትን የውል ማስከበሪያ በሙሉ የተወረሱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

36. የአገልግሎቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው ለነባራዊ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ ይህንን ይበሉ እንጂ የገንዘብ ሚ/ር ያቀረበውን ጥያቄ መሰረት ተደርጎ ጨረታ መውጣት ስለነበረበት፤ ያስያዙት የውል ማስከበሪያ ተወርሷል ለሚለውም ምን ያህል ገንዘብ ለውል ማስከበሪያ እንዲያሲዙ እና ምን ያህል ገንዘብ እንደተወረሰ የሚያሳይ ማስረጃ በሰነድ ባለመቅረቡ የተሰጡትን ምላሾች ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

37. በመሆኑም የተሽከርካሪ እና የተሽከርካሪ ጎማ ግዥዎች በወቅቱ ባለመገዛታቸው አገልግሎቱ አገልግሎት በሚሰጣቸው መ/ቤቶች ስራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

**በአገልግሎቱ የሚከናወኑ ግዥዎችን በግዥ ፍላጎት፣ በናሙናና በስፔሲፊኬሽኑ መሰረት መረከቡን በተመለከተ**

38. አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ ሲፈጽም ግዥ ጠያቂዎች በጠየቁት መሰረትና በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸው የሥራ ዝርዝር /Specification/ እና ናሙና መሰረት መሆናቸውን በማረጋገጥ ሊረከብ ይገባል፡፡

39. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- ✓ ለአምቦ ዩኒቨርስቲ እና ለሰላም ሚኒስቴር እንዲሁም ለኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን አገልግሎቱ የሚፈልጉትን ስፔስፊኬሽን ስለማያሟላ (የሚፈልጉትን የጎማ መገለጫ ቁጥር ቢነግሩም) የሚፈልጉትን የጎማ ዓይነት ስላላሟላላቸው በራሳቸው ግዥ እየፈጸሙ መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎት መስሪያ ቤቱ ስፔስፊኬሽን ዝርዝር ውስጥ ሰላም ሚኒስቴር የሚፈልገው የተሽከርካሪ ጎማ በአገልግሎቱ የስፔስፊኬሽን ዝርዝር ውስጥ ስለሌለ (ሰላም ሚኒስቴር የሚፈልገው የጎማ አይነት ስለሌለ) ግዥውን ለመፈጸም የተቸገረ መሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መግለጹ፤
  - ✓ አገልግሎቱ የተሽከርካሪ ግዥ የሚፈጽመው በቆየ (ባልተሻሻለ) ስፔስፊኬሽን መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎቱ የሚያወጣው የተሽከርካሪ ጎማ ጨረታ ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ከሚፈልጉት ጎማ ጋር የማይጣጣም መሆኑ፤
  - ✓ አገልግሎቱ በ2013 በጀት ዓመት ለሪፐብሊካን ጋርድ እና ለሰላም ሚኒስቴር አገልግሎት የሚውሉ 28 ተሽከርካሪውን ከሞኤንኮ በቀጥታ ግዥ ለመፈጸም የአሸናፊነት ደብዳቤ የተሰጠው ቢሆንም ውል ባለመፈረሙ ግዥው ያልተፈጸመ መሆኑ፤
  - ✓ ጥያቄ በማዕቀፍ ግዥ ውስጥ የማይካተቱ መኖራቸው (ጨረታ ላይ የወጣው የጎማ ዓይነት ከባለበጀት መስሪያ ቤቶች ፍላጎት ጋር ያልተጣጣመ መሆኑ)፤ እንደማሳያም ሰላም ሚኒስቴር፣ የአምቦ ዩኒቨርሲቲ እና የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የሚፈልጓቸው የጎማ አይነቶች አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥ የጎማ ዝርዝር አቅርቦት ላይ የሌለ መሆኑን መግለጻቸው፣

ከተከለሱ ሰነዶችና ከተከናወኑ ቃለ መጠይቆች ታውቋል፡፡

40. ጉዳዩን በሚመለከት ለሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ በሰጡት መልስ አገልግሎቱ ከፍተኛ የሆነ የሰው ሃይል ዕጥረት ስላለበት ሁሉንም ተቋማት ፈትሾ ለመረከብ እንደሚቸገር እና በማዕቀፍ ለሚገዙ ዕቃዎች ባለበጀት መ/ቤቶች

በስፔስፊኬሽን መሰረት መረከብ እንዳለባቸው ትዕዛዝ እንደሚሰጥ ነገር ግን የባለሙያ ዕጥረት ስላለ ለቁጥጥር እንደተቸገሩ እና በስፔስፊኬሽኑ መሰረት ርክክብ የማይደረጉ ዕቃዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡

41. የአገልግሎቱ የስራ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ በአገልግሎቱ የሚፈጸሙ የተሽከርካሪ ግዥዎች ርክክብ ሲደርግ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚ/ር ባለሙያዎች ተረጋግጦ ርክክብ የሚደረግ መሆኑ እንዲሁም በጋራ የሚያገለግሉ ዕቃዎችን /common user items including vehicle tires/ ሲሆን ካለው የሰው ኃይል ለተወሰኑ መ/ቤቶች ብቻ የሚሆን ግዥን ለመፈጸም የማይችል በመሆኑ ተቋማት በአገልግሎቱ በኩል የሚፈጸሙ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎችን አውቀው ፍላጎት እንዲልኩ የሚጠይቅ ሲሆን በአገልግሎቱ በኩል የማይፈጸሙ ግዥዎች ከሆኑ ተቋማት በራሳቸው ግዥ የሚፈጽሙ መሆኑን እና ወደፊትም በዚሁ አግባብ የሚቀጥል መሆኑን፣ ቀደም ሲል በወጡ ጨረታዎች ግዥዎችን ለመፈጸም በተደረገው ጥረት በተወሰኑ ጨረታዎች አቅራቢ ማግኘት ያልተቻለ ሲሆን በተወሰኑ ጨረታዎች ደግሞ ውል እስከመፈራረም የተደረሰ ቢሆንም ውል የፈረሙ አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለማቅረባቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የግዥ ፍላጎት ተጠይቀው የማይገዙት የተጠየቁት አጠቃላይ የጎማ መጠን በጣም አነስተኛ በመሆናቸው እነርሱን በጨረታ መግዛት አስቸጋሪ ስለሆነ በራሳቸው እንዲገዙ የሚያሳውቅ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

42. የአገልግሎቱ የስራ ሃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ለተሽከርካሪ ግዥዎች የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ባለሙያዎች ርክክብ የፈጸሙበት ሰነድ ባለመቅረቡ፤ ለተሽከርካሪ ጎማዎች / common user items including vehicle tires/ ደግሞ የሰው ሃይል የቁጥር ማነስ ብቻ ሳይሆን ቁልፍ የሚባሉ እና ባለበጀት መ/ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች የግዥ ፍላጎት ሲጠየቁ የግዥ ፍላጎት መጠየቂያ ቅጹ ፍላጎታቸውን ያማከለ መሆኑን የሚረዳ ባለሙያ ማለትም አገልግሎቱ ቁልፍ የሚባሉ የቴክኒክ ባለሙያዎችን ሳያሟላ የግዥ ሂደቱን እያከናወነ ስለሆነ፣ ከላይ የተጠቀሱት ተቋማት የጠየቁት የጎማ አይነት በጨረታው እንዳልተካተተ እና በራሳቸው እንዲገዙ ያሳወቁበት ማስረጃ ያለቅረበ በመሆኑ በተጨማሪም ውል የገቡ አቅራቢዎች እርምጃ ተወስዶባቸዋል ለሚለው ገንዘቡ ባንክ ገቢ ስለመደረጉ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ እንዲሁም ለ10 አይነት የተሽከርካሪ ጎማዎች ለአሸናፊ ተጫራቾች የአሸናፊነት ደብዳቤ (award) በአባሪ ተያይዟል ላሉት መልስ

ደግሞ የአሽናፊነት ደብዳቤ መስጠትና ግዥ መፈጸም ስለሚለያይ እና ግዥው በወቅቱ ተገዝቶ ለታለመለት አላማ ስላልዋለ ምላሹን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

43. በመሆኑም ያልተጠየቀ ግዥ (ጥራቱ ያነሰ ግዥ) እንዲፈጠር በር ከፋች ከመሆኑ በተጨማሪ መንግስት ከጥቅል ግዥ የሚያገኘውን ጥቅም ሊያሳጠው ይችላል፡፡

**አገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች በ14 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ**

44. አገልግሎቱ በማዕቀፍ የሚገዙ መለዋወጫዎችን ሲገዛ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መ/ቤቶች የግዥ ማዘዣ (perchese order) ሲደርሳቸው በሥራ ዝርዝር /Specification/ እና ናሙና መሰረት በ14 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን የሚረጋግጥበት የክትትል እና ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

45. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት

- ✓ የኦዲት ቡድኑ ለናሙና በተመረጡ ባለበጀት መስሪያቤቶች ማለትም ለኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን፣ ለሰላም ሚኒስቴር፣ ለገቢዎች ሚኒስቴር እና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባደረገው ቃለ-መጠይቅ አገልግሎቱ በማዕቀፍ የሚገዙ መለዋወጫዎችን ማለትም የተሽከርካሪ ጎማዎችን ሲገዛ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መ/ቤቶች የግዥ ማዘዣ (perchese order) ሲደርሳቸው በሥራ ዝርዝር /Specification/ እና ናሙና መሰረት በ14 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን የሚረጋግጥበት የክትትል እና ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ እና እስካሁንም ድረስ ለባለበጀት መስሪያ ቤቶች አንድም የጎማ ግዥ ያልፈጸመ መሆኑ እንዲሁም ባለበጀት መ/ቤቶች ግዥ እንዲገዛላቸው በተደጋጋሚ ቢጠይቁም በወቅቱ ምላሽ ባለመስጠቱ እና እስከ ግንቦት እና ሰኔ ወር ድረስ (የበጀት መዝጊያ ወር ድረስ) ምላሽ ባለመስጠቱ ለተሽከርካሪ ጎማ የሚመደበው በጀት እስከመቃጠል የሚደርስበት አጋጣሚ መኖሩን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን እና የገቢዎች ሚኒስቴር የሥራ ሃላፊዎች መግለጻቸው፤
- ✓ አገልግሎቱ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የባለበጀት መስሪያ ቤቶችን አቅራቢዎች ለማቅረብ የተወዳደሩበት መስፈርት (specification) ስላላቀረበላቸው የተሽከርካሪ ጎማ ለመግዛት የተቸገሩ መሆኑ፤

ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ታውቋል፡፡

46. የአገልግሎት መ/ቤቱ የስራ ሃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው ለነባራዊ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ እስካሁን ድረስ ለባለበጀት መ/ቤቶች አንድም ጎማ ግዥ በአገልግሎቱ በኩል ባይገዛም እያንዳንዱ ባለበጀት መ/ቤቶች በተናጥል ጥያቄ እያቀረቡ ግዥ መፈጸማቸው ለዚህም ምክንያቱ ግዥ ጠያቂዎች የሞዴልና የብራንድ ለውጥ እንዲደረግላቸው የሚጠይቁ መሆኑን፤ ባለበጀት መ/ቤቶች(በናሙና ከታዩት ውስጥ) የተሽከርካሪ ጎማ በአገልግሎቱ የስፔሰፊኬሽን ዝርዝር ሰለሌለ ለመግዛት የተቸገሩ ሰለመሆኑ ደግሞ በአገልግሎቱ የሚፈጸሙ የተሽከርካሪ ግዥዎች ርክክብ ሲደረግ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚ/ር ባለሙያዎች ተረጋግጦ ርክክብ የሚፈጸም ሲሆን የተሽከርካሪ ጎማ ግዥን በተመለከተ በባለበጀት መ/ቤቶች በወጣው ስፔሰፊኬሽን መሰረት መሆኑን አረጋግጠው እንዲረከቡ በሰርኩላር የሚያስተላልፉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

47. በመሆኑም ባለበጀት መ/ቤቶች የጠየቁትን ተሽከርካሪ እና ጎማ በወቅቱ አግኝተው ካልተጠቀሙበት ስራቸውን በአግባቡ እንዳይፈጽሙ እንቅፋት ሊፈጥር ይችላል፡፡

**አገልግሎቱ አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ (liquidity damage) ማስከፈሉን በተመለከተ**

48. አገልግሎቱ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪ፣ ጎማዎችን እና መለዋወጫዎችን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ (liquidity damage) ሊያስከፍል እና አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

49. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ✓ በናሙና ተመረጠው በታዩ ተቋማት ማለትም በገቢዎች ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን፣ በሰላም ሚኒስቴር፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በገንዘብ ሚኒስቴር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ የጉዳት ካሳ የሚወሰነው በአገልግሎት መስሪያ ቤቱ በኩል መሆኑ እና አቅራቢ ድርጅቶች መለዋወጫዎችን እና ተሽከርካሪዎችን ሲያቀርቡ በከፍተኛ ሁኔታ መዘግየት በታይባቸውም የጉዳት ካሳ ያልተቀጡ መሆኑን የገለጹ መሆኑ፣ እና

✓ ለናሙና በተመረጡ ተቋማት ከ2012 በጀት ዓመት ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ በአገልግሎቱ በኩል አንድም የጎማ ግዥ ያልተገዛ መሆኑን

ለማወቅ ተችሏል፡፡

50. ጉዳዩን በሚመለከት የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ለማጠቃለያ ጥያቄ በሰጡት መልስ አገልግሎቱ የሚፈራረመው ለሶስት ዓመት መሆኑን ጠቅሰው የክትትል ድክመት እንዳለ እና ለክትትሉም የሚያግዝ ዝርዝር መመሪያ እንደሌለ ጠቅሰው ሶስት ዓመት ጠብቀው ፐርፎርማንስ ቦንድ እንደሚወስዱ ገልጸዋል፡፡

51. የአገልግሎቱ የስራ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው ለነባራዊ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ የኦዲት ግኝቱን አምነው ክፍያ የሚፈጸመው በባለበጀት መ/ቤቶች በኩል ስለሆነ አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን ካልተወጡ የጉዳት ካሳ ለማስከፈል አስቸጋሪ በመሆኑ ያስያዙት የውል ማስከበሪያ የሚወረስ መሆኑን በምሳሌነት ማክ ኢንተርናሽናል እና ጥላሁን ጫላ የተባሉ አቅራቢዎችን እንደ ማሳያ ጠቅሰዋል፡፡

52. የአገልግሎቱ የስራ ኃላፊዎች ለነባራዊ መግለጫ በሰጡት መልስ ይህንን ቢሉም የተጠየቀው የጉዳት ካሳ ቅጣት እንጂ የውል ማስከበሪያ መወረስን አስመልክቶ ባለመሆኑ እንዲሁም የተጠቀሱት ተቋማት የውል ማስከበሪያ የተወረሰበትን በማስረጃ አስደግፈው ባለማቅረባቸው እንዲሁም ዝርዝር መመሪያ አስፈላጊ ከሆነም አዘጋጅተው በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ሥራ ላይ ማዋል ስለነበረባቸው የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

53. በመሆኑም አገልግሎት ፈላጊዎቹ የፈለጉትን ዕቃ በወቅቱ አለማግኘታቸው በሥራቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማስከተሉም በላይ መንግስት ከጉዳት ካሳ ክፍያ (liquidity damage) የሚያገኘውን ጥቅም ከማሳጣቱ በተጨማሪ አቅራቢዎች ከጥፋታቸው እንዳይታረሙ ምክንያት ሆኗል፡፡

**አገልግሎቱ የተሽከርካሪዎችን ግዥ ሲፈጽም መለዋወጫዎቹ እና የጥገና አገልግሎት ተደራሽነትን ከግምት ውስጥ ማስገባቱን በተመለከተ**

54. አገልግሎቱ የተሽከርካሪዎችን ግዥ ሲፈጽም መለዋወጫዎቹ በሚፈለገው የአቅርቦት መጠን እና የጥገና አገልግሎት ተደራሽነትን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ✓ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪ ግዥን በተመለከተ የባትሪ መሙያ ጣቢያዎች (Charging centers)፣ ከጥገና አገልግሎት፣ መለዋወጫና ኢንሹራንስ ጋር በተያያዘ ቅድመ ዝግጅት ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ አገልግሎቱ በ2015 በጀት ዓመት ለባለበጀት መ/ቤቶች አገልግሎት የሚውል የተሽከርካሪ ችግርን ለመቅረፍ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ሲገዛ የሚገጥሙ ችግሮችን ማለትም ከኢንሹራንስ፣ የጥገና (መለዋወጫዎቹ በሚፈለጉት መጠን መገኘታቸውን) እና ቻርጅ አገልግሎት ችግር አለመኖሩን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ (የአዋጭነት ጥናት ሳያጠና) አወዳድሮ ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ አቅራቢዎች የአሸናፊነት እውቅና (Award) የሰጠ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ሰነዶችና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ታውቋል፡፡

56. የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ፤ የኢንሹራንስ፣ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ እና የአዋጭነት ጥናት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ስፔስፊኬሽን በሚያዘጋጀው የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚ/ር መሆኑን ጠቅሰው በአገልግሎቱ በኩል ግን ከጥገና እና መለዋወጫ ጋር የተያያዙ ጉዳይዎች በጨረታ ሰነዱ ላይ በግልጽ ተቀምጠው መስፈርቱን ያሟሉ እና ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ ተጫራቾች የአሸናፊነት ደብዳቤ የተሰጣቸው መሆኑን፣ በ2015 በጀት አመት ጨረታ ከወጣላቸው ውስጥ አቅራቢ የተገኘላቸው 236 ተሽከርካሪዎች በመሆናቸው እና 228 በኤሌክትሪክ ነዳጅ ስለሚሰሩ ወደ አገር ውስጥ ተሽከርካሪዎቹ ከመግባታቸው በፊት ቻርጅ የሚደረጉበት መሰረተ ልማት መሞላት ስለሚያስፈልግ የተቋማቱ ድርሻ እንዲገለጽ እና በየተቋሙ የሚተከለውን የቻርጅ ማድረጊያ ስቴሽን ብዛት ለመወሰን የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ እንዲቻል የገንዘብ ሚኒስቴርን በድብዳቤ ቁጥር ግንግ/ሰሀ/ግዥ/66/09 በ03/01/2016 የገንዘብ ሚኒስቴርን መጠየቃቸውን ገልጸዋል፡፡

57. የበላይ ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ይህንን ይበሉ እንጂ የአገልግሎቱ የግዥ ሥራ አስፈጻሚ ለማጠቃለያ ጥያቄ የሰጡት መልስ ጋር የተለያየ በመሆኑ የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

58. ስለሆነም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ግዥ ቅድመ ዝግጅት መኖሩ ሳይረጋገጡ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች እንዲገዛ ማድረጋቸው ቻርጅ ማድረጊያ ከማጣትና ከጥገና ከማግኘት ችግር የተነሳ የታለመላቸውን አላማ እንዳያሳኩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አገልግሎቱ በኢፌዴሪ የግዥና ንብረት ባለስልጣን እና ከኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት በተገኘው የገበያ ዋጋ ጋር ማነፃፀሩን በተመለከተ**

59. አገልግሎቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የግዥና ንብረት ባለስልጣን (በቀድሞው ኤጀንሲ) እና ከኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት (የቀድሞው የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ) በተገኘው የገበያ መረጃና አቅራቢዎች ከጠየቁት ዋጋ ጋር ሊያነጻጽር ይገባል፡፡

60. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ✓ አገልግሎቱ በ2013 በጀት ዓመት በጨረታ ሰነድ ቁጥር PPPDS/MOA/LCB/PG/ 150/12/20 ለግብርና ሚኒስቴር የሞተር ሳይክል ግዥ ለመፈጸም ጨረታ የወጣ ቢሆንም የገበያ ዋጋ ጥናት አልቀረበም ተብሎ ግዥው የተሰረዘ መሆኑ፤
- ✓ በ2014 በጀት ዓመት በቁጥር 39 የሚሆኑ የተሽከርካሪ ጎማዎች ግዥ በወጣው ጨረታ ለ2 ጎማዎች የገበያ ዋጋ አልተገኘም ተብሎ የግዥ ሂደቱ የተሰረዘ መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎቱ ከማዕከላዊ ስታስቲካል ኤጀንሲ መረጃን በወቅቱ ያለማግኘትና የወቅቱን ገበያ ዋጋ ያላማከለ የገበያ መረጃ እንደሚቀርብ አገልግሎቱን በበላይነት በሚያስተዳድረው ቦርድ ቃለ-ጉባኤ የተገለጸ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

61. የአገልግሎቱ የስራ ሃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው ለነባራዊ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ የኦዲት ግኝቱን ተቀብለው ቀደም ሲል የገበያ ዋጋ መረጃ ጥራትና በወቅቱ ያለማቅረብ ችግሮች የነበሩ መሆኑን ጠቅሰው በአሁኑ ሰዓት ተቀራርቦ የመስራት ሁኔታ መፈጠሩ እና ችግሮቹ መሻሻላቸውን ገልጸዋል፡፡

62. በመሆኑም አሁናዊ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫ ዋጋ እና አቅራቢው የሚያቀርበው መለዋወጫ እና ተሽከርካሪ ዋጋ ስለማይጣጣም ተጫራቾች እንዳይወዳደሩ ከማድረጉ በተጨማሪ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫ ግዥዎች እንዲቋረጡና ከገበያው

ዋጋ በላይ የተጋነነ መንግስት ወጪ እንዲያወጣ እና ተቋሙ የተቋቋመበትን አላማ እንዳያሳካ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አገልግሎቱ የጨረታ ማስታወቂያው ለህዝብ በይፋ ያወጣ መሆኑን በተመለከተ**

63. አገልግሎቱ የግዥ ዕቅዱን እንደግዥው ዓይነት የጨረታ ማስታወቂያውን በአገልግሎቱና በግዥና ንብረት ባለሥልጣን ድህረ-ገጽና በመንግስታዊ ጋዜጣ እንዲወጣ ሊያደርግ ይገባል፡፡

64. ይሁን እንጂ መረጃን ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ድረ-ገጽ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም ከ2015 ዓ.ም ይህ የኦዲት ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የአገልግሎቱ ድህረ-ገጽ ከሚያስተዳድረው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሰርቨር ችግር ስላጋጠመው የተቋረጠ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ታውቋል፡፡

65. የአገልግሎቱ የስራ ሃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው ለነባራዊ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ በወቅቱ ችግር እንዳለ ጠቅሰው በአሁኑ ሰዓት ድረ-ገጹን እያስተካከሉ እና የመስሪያቤቱን ሎጎ እያሰሩ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

66. የአገልግሎቱ የበላይ ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ የድህረ-ገጽ ችግር መኖሩን ተቀብለው ነገር ግን በግዥ አፈጻጸም መመሪያ ላይ የጨረታ ማስታወቂያ አገልግሎቱ ድህረ-ገጽ ላይ መልቀቅ አስገዳጅ አለመሆኑን ገልጸው ሆኖም ግን በአገልግሎቱ የሚፈጽሙት የስትራቴጂክ እና የማዕቀፍ ግዥዎችን በኢ.ቢ.ሲ ቴሌቭዥን እያስነገሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

67. የአገልግሎቱ የበላይ ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ይህንን ይበሉ እንጂ በአገልግሎቱ የግዥ የውስጥ አሰራር መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 4 የጨረታ ማስታወቂያውን በአገልግሎቱና በግዥና ንብረት ባሥልጣን ድህረ-ገጽና በመንግስታዊ ጋዜጣ ማውጣት እንዳለበት ስለተደነገገ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ይቸገራል፡፡

68. በመሆኑም አገልግሎቱ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች የሚወጡ ጨረታዎችን ተደራሽነት ስለሚያሳጣ ብዙ ተወዳዳሪ እንዳይገኝ እንቅፋት ሆኗል፡፡

አገልግሎቱ የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እና ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት የዘረጋ መሆኑን በተመለከተ

69. አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫ ግዥ እንዲፈጸምላቸው ከሚጠይቁ መ/ቤቶች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እና ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

70. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

- ✓ አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫ ግዥ እንዲፈጸምላቸው ከሚጠይቁ መ/ቤቶች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ የማይሰጥ መሆኑና ተጠቃሚ መ/ቤቶች ለአገልግሎት መ/ቤቱ ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርቡም አገልግሎቱ ለተጠየቀው ጥያቄ ቶሎ ምላሽ የማይሰጥ እና መልስ የሚሰጥ ደግሞ ከብዙ ወራት በኋላ መሆኑን ለናሙና በተመረጡ መ/ቤቶች ማለትም የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን እና የሰላም ሚኒስቴር እንዲሁም አምቦ ዩኒቨርስቲ እና ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሰቲ የስራ ሃላፊዎች መግለጻቸው፡፡
- ✓ አገልግሎቱ በየሶስት ወሩ ከግዥ ተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች፣ ከአቅራቢዎችና ሌሎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትጋር የጋራ መድረክ ቢኖረውም በዚህ የጋራ መድረክ አገልግሎቱ በሚሰራቸው ስራዎች ላይ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ በአፈጻጸም ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ላይ ውይይት በማድረግ የጋራ መፍትሄ የመስጠት ስራዎች እንደሚሰሩ የተገለጸ ቢሆንም በጋራ መድረኩ ላይ አብዛኛውን ጊዜ የሚገኙት በቀጥታ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ሳይሆን ቡድን መሪ ወይም ባለሙያዎችን የመላክ ችግር እንደሚታይ እና ይህ ደግሞ በአፈጻጸም ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ላይ ውይይት በማድረግ የጋራ መፍትሄ ማስቀመጥና ተግባራዊ ማድረግ ላይ ክፍተቶች የገጠሙ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡ (በአገልግሎቱ ቃለ-ጉባኤ ቁጥር 118/2015 ገጽ 10 የተገለጸ መሆኑ፣

  በኦዲቱ ታውቋል፡፡

71. የአገልግሎቱ የስራ ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ የተሽከርካሪ ግዥ ጥያቄን በተመለከተ ያላቸው ግንኙነት ከገንዘብ ሚ/ር ጋር መሆኑን ጠቅሰው ክፍተት የሌለ መሆኑን እና የተሽከርካሪ ጎማ ግዥን በተመለከተ ደግሞ በበጀት ዓመቱ አጋማሽ ድረስ ግዥው የማይፈጸም ከሆነ ተቋማት በራሳቸው ግዥ እንዲፈጽሙ እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

72. የአገልግሎቱ የስራ ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ይህንን ይበሉ እንጂ አገልግሎቱ የግዥ አዋጁንና የግዥ መመሪያውን ተከትሎ በየአመቱ ከተቋማት የግዥ ፍላጎት እየሰበሰቡ አመታዊ የማዕቀፍ ግዥ ዕቅድ ማዘጋጀትና ግዥውን መፈጸም በእነርሱ በኩል የማይገዛ ከሆነም ወዲያው ለባለ በጀት መ/ቤቶች ማሳወቅ ስላለባቸው ምላሹን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

73. ስለሆነም ሁኔታው የባለበጀት መ/ቤቶችን የበጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የበጀት መቃጠል ስለሚያስከትል በመስሪያ ቤቶቹ አጠቃላይ ስራ ላይ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡

**አገልግሎቱ የተገልጋዮችን አቤቱታና ቅሬታ ተቀብሎ መልስ መስጠቱን በተመለከተ**

74. አገልግሎቱ የተገልጋዮችን አቤቱታና ቅሬታ ተቀብሎ ባስቀመጠው የግዜ ገደብ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡

75. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች

- አገልግሎቱ የተሸከርካሪ እና መለዋወጫ ግዥ እንዲፈጸምላቸው ከሚጠይቁ መ/ቤቶች ጋር የተገልጋዮችን አቤቱታና ቅሬታ ተቀብሎ ምላሽ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ያላስቀመጠ እና
- ለናሙና በተመረጡ ባለበጀት መ/ቤቶች ማለትም በሰላም ሚኒስቴር፣ በገቢዎች ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ባለስልጣን፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በገንዘብ ሚኒስቴር በኦዲት ቡድኑ በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ እንደተቻለው የተሸከርካሪ ጎማ ለመግዛት በተደጋጋሚ ቢጠይቁም አገልግሎቱ ወቅታዊ ምላሽ የማይሰጥ መሆኑ እና ከ 4 ወርና ከ 5 ወር በኋላ (በጀት መዝጊያ ወር ሲደርስ) ባለበጀት መ/ቤቶችን በራሳቸው ግዥ እንዲፈጽሙ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑ በዚህም ምክንያት ጊዜው ካለቀ በኋላ ምላሽ ስለሚሰጣቸው ትክክለኛውን የጨረታ ዘዴ የማይጠቀሙ መሆኑ (ለአብነትም በሰላም ሚኒስቴር የተሸከርካሪ ጎማ ግዥ ሲፈጽም ውስን ጨረታ መጠቀም እያለበት የዋጋ ማቅረቢያ ዘዴ (ፕሮፎርማ) የተጠቀሙ መሆኑን መግለጻቸው፤ ለምሳሌ
    - የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን በደብዳቤ ቁጥር ኢት/ቡ/ሻ/ባ/መ-30//28/ በቀን ሐምሌ 9/2013 ዓ.ም በማዕቀፍ ጥቅል ግዥ አቅራቢ ይገኛል ተብሎ ለ1 ዓመት ያህል ሲጠብቁ ቆይተው የግዥ ሂደቱ ባለመጠናቀቁ በራሳቸው እንዲገዙ ሐምሌ 26/2013 የግዥ ትዕዛዝ መሰጠቱ፤

➢ አምቦ ዩኒቨርስቲ በአገልግሎቱ በቀን መስከረም15/2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት ከተላከላቸው የጎማ ዓይነቶች ውስጥ ለዩኒቨርስቲው የሚሆን 10 አይነት ጎማዎችን መርጠው ያቀረቡ ሲሆን ነገር ግን እስከ ሐምሌ 30/2013 ዓ.ም ድረስ በማዕቀፍ ግዥ ተፈጽሞ ግዥ ያልተገለጸላቸው በመሆኑ ዩኒቨርስቲው ከፍተኛ የጎማ ችግር የገጠመው መሆኑ እና ነሐሴ 6/2013 ዓ.ም በራሳቸው እንዲገዙ የታዘዘ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

76. የአገልግሎቱ የስራ ሃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው ለነባራዊ መግለጫ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና ለረቂቅ ሪፖርቱ በጽሁፍ በሰጡት ምላሽ የተሽከርካሪ ግዥ ጥያቄን በተመለከተ ያላቸውን ግንኙነት ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር መሆኑ እና በዚህ ረገድ ክፍተት የሌለ መሆኑን ገልጸው የተሽከርካሪ ጎማ ግዥን በተመለከተ የበጀት ዓመቱ አጋማሽ ድረስ ግዥው የማይሳካ ከሆነ ተቋማት በራሳቸው ግዥውን እንዲፈጽሙ እያደረጉ እንደሚገኙ ጠቅሰዉ በተለይ አዳዲስ አመራር ከመጣ በኋላ ለተጠቃሚ መስሪያ ቤቶች የሚሰጡበትን የጊዜ ስታንዳርድ በማውጣት እያንዳንዱ ባለበጀት መ/ቤት ለሚያቀርበው ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ እየሰጡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

77. የአገልግሎቱ የስራ ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ይህንን ይበሉ እንጂ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ምላሹን ለመቀበል ይቸገራል፡፡

78. በመሆኑም ባለበጀት መ/ቤቶች ስራ እንዳይሰሩ ምክንያት ከመሆኑ በተጨማሪ መንግስት ከጥቅል ግዥ የሚያገኘውን ጥቅም አሳጥቷል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሀሳቦች

79. አገልግሎቱ የተሽከርካሪና የመለዋወጫ ግዥዎችን ለማከማናወን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚከናወንበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት የመደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

- የአገልግሎቱን የውስጥ አፈጻጸም መመሪያዎች ያልተሻሻሉ መሆናቸው፣ አገልግሎቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ በህግ በተቀመጠው አግባብ በወር አንድ ጊዜ የማይሰበሰብ መሆኑ፣
- አገልግሎቱ የግዥ አገልግሎት ጠያቂ መ/ቤቶች ግዥ በሚጠይቁበት ጊዜ በበጀት ማስደገፋቸውን የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎችን ግዥ ሂደት ሲፈጽም አገልግሎት ጠያቂዎች የሚፈልጉበትን ጊዜ እና መጠን ከግንዛቤ አላስገባም/ ግዥው የሚዘገይ መሆኑ፡፡
- የመንግስት ተቋማት የሚጠይቁት የጎማ ግዥ ጥያቄዎች በአገልግሎቱ በሚያወጣው በጨረታ ውስጥ ያልተካተቱ መኖራቸው፣
- አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ ሲፈጽም በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸው የሥራ ዝርዝር /Specification/ እና ናሙና መሰረት ማቅረባቸውን በራሱ የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- አገልግሎቱ በማዕቀፍ የሚገዙ መለዋወጫዎችን ሲገዛ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መ/ቤቶች የግዥ ማዘዣ (perchese order) ሲደርሳቸው በሥራ ዝርዝር / Specification / እና ናሙና መሰረት በ14 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን የሚረጋገጥበት የክትትል እና ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- አገልግሎቱ አቅራቢዎች በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎችን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ (liquidity damage) አላስከፈለም፡፡

- አገልግሎቱ የተሽከርካሪዎችን ግዥ ሲፈጽም ዋጋቸው ተመጣጣኝ መሆኑን ፤ መለዋወጫዎቹ በሚፈለገው የአቅርቦት መጠን እና የጥገና አገልግሎት ተደራሽነትን ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም፡፡
- አገልግሎቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የግዥና ንብረት ባለስልጣን (በቀድሞው ኤጀንሲ) እና ከኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት (የቀድሞው የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ) በተገኘው የገበያ መረጃና አቅራቢዎች ከጠየቁት ዋጋ ጋር አያነጻጽርም፡፡
- አገልግሎቱ የግዥ ዕቅዱን እንደ ግዥው ዓይነት የጨረታ ማስታወቂያውን በአገልግሎቱ ድህረ-ገጽ እንዲወጣ አላደረገም፡፡
- አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫ ግዥ እንዲፈጸምላቸው ከሚጠይቁ መ/ቤቶች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እና ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት በመዘረጋ ተግባራዊ አላደረገም፡፡
- አገልግሎቱ የተገልጋዮችን አቤቱታና ቅሬታ ተቀብሎ ባስቀመጠው የግዜ ገደብ ምላሽ አልሰጠም፡፡

80. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

81. በአዲቱ ወቅት አገልግሎቱ የመንግስት ተሽከርካሪና መለዋወጫዎች ግዥ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

- ➢ አገልግሎቱ የሚጠቀምባቸውን የአሰራር መመሪያዎች አሁን እየተሻሻለ በሚገኘው የግዥ አዋጅ መሰረት እንዲጣጣሙ በማድረግ መክለስ በቦርዱ ማጸደቅ ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም በሥራ ላይ ባለው የግዥ መመሪያ ያልተሸፈኑ የጉዳት ካሣ ክፍያ አከፋፈል፣ ዕቃዎችን በማዕቀፍ ለመግዛት አስፈላጊ የሆነው አነስተኛ ብዛት የመሳሰሉት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በማሳወቅና ግብዓት በመስጠት እንዲካተቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ➢ አገልግሎቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ በህግ በተቀመጠው መሰረት በየወሩ በመሰብሰብ የአገልግሎቱን አፈጻጸም መገምገምና የሚቀርቡለትን የተለያዩ መመሪያዎች መርምሮ ሊያጸድቅ ይገባል፡፡
- ➢ አገልግሎቱ ለሚፈጽማቸው የተሽከርካሪ ግዥዎች የግዥ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር ለግዥዎቹ በቂ በጀት መያዙን ማረጋገጥ፤ በማዕቀፍ ለሚገዙ ግዥዎች ደግሞ ግዥውን ከጠየቀው መስሪያ ቤት ጋር በመቀናጀት በበጀት መደገፋቸውን በማረጋገጥ የግዥ ሂደቱ በሚፈለገበት ጊዜና መጠን እና በተያዘው በጀት በመፈጸም የቀረበው ዋጋ ደግሞ ከተያዘው በጀት በላይ ከሆነ ግዥን ከጠየቀው አካል ጋር በመመካከር በመወሰን የተቋቋመበትን አላማ ሊያሳካ ይገባል፡፡
- ➢ አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ ሲፈጽም ሁሉም የመንግስት ተቋማት የጠየቁትን ግዥ መሰረት ያደረገ ዝርዝር ስፔስፊኬሽን በባለሙያ በማዘጋጀት ጨረታ ሊያወጣና ውድድሩን አሸንፈው እንዲያቀርቡ ከተመረጡት ጋር ውል የገባባቸውን ንብረቶች በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸው የሥራ ዝርዝር /Specification/ እና ናሙና መሰረት መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ለተግባራዊነቱም ክትትል የሚያደርግበት፣ እንዲሁም በማዕቀፍ የሚገዙ መለዋወጫዎችንና ጎማዎች አቅራቢ ድርጅቶች


ከተጠቃሚ መ/ቤቶች የግዥ ማዘዣ (perchese order) ሲደርሳቸው በሥራ ዝርዝር /Specification/ እና ናሙና መሰረት በ14 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን የሚረጋግጥበት የክትትል እና ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ እንዲሁም አሰራሩን በመገምገም እና ተጨራቾች ለጨረታ የማይቀርቡበትን ሁኔታ አጥንቶ የመፍትሄ ሃሳብ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- አገልግሎቱ ተሽከርካሪና የተሽከርካሪ መለዋዋጫዎችን ግዥ ሲፈጽም በግልጽ ጨረታ መገዛት ያለበት ግዥ ከግልጽ ጨረታ ውጭ ግዥ ለማከናወን ዝርዝር ምክንያቱን ሥልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ ፈቃድ ሊያገኝ ይገባል፡፡
- አገልግሎቱ ውድድሩን አሸንፈው አሸናፊ የተደረጉና ውል የገቡ አቅራቢዎች በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎችን በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ (liquidity damage) የሚቀጡበትን አግባብ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከገንዘብ ሚኒስቴር እና የመንግስት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን ጋር በመመካከር ውል በገባው በአገልግሎቱና ክፍያ በሚፈጽሙ ባለበጀት መ/ቤቶች የተፈጠረውን የትግበራና የህግ ክፍተት ሊያስተካከል እና የሚቀጡበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- አገልግሎቱ የተሽከርካሪዎችን ግዥ ሲፈጽም ዋጋቸው እና አገልግሎታቸው ተመጣጣኝ እንዲሆን ከሃገሪቱ ነባራዊ እና የአየር ሁኔታ የተጣጣሙ እንዲሆኑ፤ የመለዋወጫ አቅርቦት በሃገር ውስጥ መኖሩንና የጥገና አገልግሎትን ተደራሽነት ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ሲሆኑ ደግሞ ባትሪያቸውን የሚሞሉበት (Charging centers) ጣቢያዎች መኖራቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት በጥናት ተመርኩዞ መግዛት ይኖርበታል፡፡
- አገልግሎቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የግዥና ንብረት ባለስልጣን እና ከኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የተገኘው የገበያ መረጃ በየጊዜው በመሰብሰብ በማደራጀትና አቅራቢዎች ከሰጡት ዋጋ ጋር በማነጻጸር ለግዥ ሂደቱ በግብዓትነት ሊጠቀም ይገባል፡፡
- አገልግሎቱ የግዥ ዕቅዱን እንደግዥው ዓይነት የጨረታ ማስታወቂያውን በአገልግሎቱና በግዥና ንብረት ባሥልጣን ድህረ ገጽ እንዲወጣ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫ ግዥ እንዲፈጸምላቸው ከሚጠይቁ መ/ቤቶች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እና ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግና የተገልጋዮችን አቤቱታና ቅሬታ ተቀብሎ ባስቀመጠው የግዜ ገደብ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡

በመጨረሻም ለኢትዮጵያ የመንግስት ግዥ አገልግሎት የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ለታዩ የመንግስት ተቋማት ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1፡ የኢፌዴሪ መንግስት ግዥ አገልግሎት ድርጅታዊ መዋቅር



# አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡- <u>የመንግስት ግዥ አገልግሎት</u>

የኦዲት አካባቢ፡- <u>የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ አፈፃፀም ውጤታማነትን መገምገም</u>

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች |
|---|---|
| 1.አገልግሎቱ የሚያከናውናቸው የተሽከርካሪና የተሽከርካሪ መለዋወጫ ግዥዎች በግዥ ደንብና መመሪያ እንዲሁም በኮንትራት ዉሎች መሰረት የሚገዛበት፣ የሚረከብበት እና የሚያከፋፍልበትን የአሰራር ስርዓት መገምገም፡፡ | 1. አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫ ግዥን ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት ሊኖረው ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 ገጽ 4864 |
| | 2. አገልግሎቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ የአገልግሎቱን ስትራቴጂዎችና የአፈጻጸም መመሪያዎች በማዘጋጀት በሚመለከተው አካል ሊያጸድቅና ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የመንግስት ግዥ አገልግሎት መቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 184/2002 ቁጥር 9 ንዑስ ቁጥር 2 ገጽ 4 |
| | 3. አገልግሎቱን በበላይነት የሚያስተዳድረው ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ሊሰበሰብ ይገባል::<br>ምንጭ፡- ደንብ ቁጥር 184/2002 ቁጥር 10 ንዑስ ቁጥር 1 |
| | 4. አገልግሎቱ ከብር 100,000,000 በላይ ለሆኑ ግዥዎች የግምገማ ውጤቱን ለቦርዱ ሊያቀርብ እና በ 5 ቀን ውስጥ በቦርዱ ሊያጸድቅ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የግዥና የውል አስተዳደር የውስጥ አሰራር መመሪያ ገጽ6 አንቀጽ 7 ንዑስ ቁጥር 10 |
| | 5. አገልግሎቱ የግዥ አገልግሎት ጠያቂ መ/ቤቶች ግዥ በሚጠይቁበት ጊዜ በበጀት መደገፉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የግዥና የውል አስተዳደር የውስጥ አሰራር መመሪያ ገጽ 6 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 |
| | 6. አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎችን ግዥ ሂደት ሲፈጽም አገልግሎት ጠያቂዎች ያላቸውን በጀት ፣ የሚፈልጉበትን ጊዜ እና መጠን ከግንዛቤ ሊያስገባ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-መልካም ተሞክሮ |
| | 7. አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎችን ግዥ ሲፈጽም ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት ቀድሞ የነበረውን የመልካም ስራ አፈጻጸም የሚገመግምበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የመንግስት ግዥ አፈጻጸምመመሪያ ቁጥር 43/2003 ገጽ 38 |
| | 8. አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎች ግዥ ሲፈጽም ውል የገባባቸውን ንብረቶች በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለጸው የሥራ ዝርዝር /Specification/ እና ናሙና መሰረት መሆናቸውን በማረጋገጥ ሊረከብ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | ምንጭ፡- የግዥና የውል አስተዳደር የውስጥ አሰራር መመሪያ ገጽ10 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ6 |
| | 9. አገልግሎቱ ከግልጽ ጨረታ ውጪ ሌሎች የግዥ ዘዴዎችን ሲከተል የግዥ ዘዴው የተመረጠበትን ምክንያት ሊገልጽ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ23 ንዑስ አንቀጽ1 ቁጥር 6 ገጽ4872 |
| | 10. አገልግሎቱ በማዕቀፍ የሚገዙ መለዋወጫዎችን ሲገዛ አቅራቢ ድርጅቶች ከተጠቃሚ መ/ቤቶች የግዥ ማዘዣ (perchese order) ሲደርሳቸው በሥራ ዝርዝር / Specification / እና ናሙና መሰረት በ14 ቀን ውስጥ ማቅረባቸውን የሚረጋገጥበት የክትትል እና ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- General condition of the contract page 13(GCC27.1) |
| | 11. አገልግሎቱ አቅራቢዎች በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪ እና መለዋወጫዎችን አጠናቀው በማያስረክቡ አቅራቢዎች ላይ ላዘገዩበት ጊዜ ባቀረበው የውል መጠን በየቀኑ 0.1% የጉዳት ካሳ (liquidity damage) ሊያስከፍል እና አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- General condition of the contract page 15(GCC54.1) |
| | 12. አገልግሎቱ የሚፈጽማቸው የተሽከርካሪ እና መለዋወጫ ግዥዎች በበጀት እቅድ የተደገፈና የተከናወነው ግዥ የባለበጀት መ/ቤቶችን (የተጠቃሚዎችን) ፍላጎት መሰረት ያደረገ እና ለተፈለገው አላማ የሚውል ሊሆን ይገባል፡፡ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀፅ 4 ገፅ 4865 |
| | 13. አገልግሎቱ ተሽከርካሪዎችን ሲረከብ በጊዜያዊነት ለሚያቆይበት መጠለያ (ተሽከርካሪዎችን ከዝናብና ከፀሀይ የሚከላከል) ሊኖረው ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የግዥና የውል አስተዳደር የውስጥ አሰራር መመሪያ ገጽ7 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ9 |
| | 14. አገልግሎቱ የተሽከርካሪዎችን ግዥ ሲፈጽም ዋጋቸው ተመጣጣኝ መሆኑን ፣ መለዋወጫዎቹ በሚፈለገው የአቅርቦት መጠን እና የጥገና አገልግሎት ተደራሽነትን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ |
| 1. አገልግሎቱ የተሽከርካሪና መለዋወጫ ግዥን በብቃት ለመወጣት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና | 15. አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫ ግዥ ወጪ ቆጣቢ ፣ ግልፅ እና ዘመናዊ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 31 ገፅ 4878<br>16. አገልግሎቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የግዥና ንብረት ባለስልጣን (በቀድሞው ኤጀንሲ) እና ከኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት (የቀድሞው የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ) በተገኘው የገበያ መረጃና አቅራቢዎች ከጠየቁት ዋጋ ጋር ጋር ሊያነጻጽር ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፡፡ | ምንጭ፡- የግዥና የውል አስተዳደር የውስጥ አሰራር መመሪያ ገጽ6 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 |
| | 17. አገልግሎቱ የግዥ ዕቅዱን እንደ ግዥው ዓይነት የጨረታ ማስታወቂያውን በአገልግሎቱና በግዥና ንብረት ባሥልጣን ድህረ ገጽና በመንግስታዊ ጋዜጣ እንዲወጣ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የግዥና የውስጥ አሰራር መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ ቀንቀጽ4 ገጽ7 |
| | 18. አገልግሎቱ በአለም አቀፍ ጨረታ (ICB) የሚፈጽማቸውን ግዥዎች ሌተር ኦፍ ክሬዲት (LC) በመክፈት ተሸከርካሪና መለዋወጫው ከተጫነበት አንስቶ እስከ ርክክብ ያለውን ሂደት እየተከታተለ ለተጠቃሚ መ/ቤቶች ሊያሳውቅ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የግዥና የውል አስተዳደር የውስጥ አሰራር መመሪያ ገጽ10 አንቀጽ 3ንዑስ አንቀጽ 3 |
| | 19. አገልግሎቱ የተሽከርካሪ እና መለዋወጫ ግዥ እንዲፈጸምላቸው ከሚጠይቁ መ/ቤቶች ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እና ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ |
| | 20. አገልግሎቱ የተገልጋዮችን አቤቱታና ቅሬታ ተቀብሎ ባስቀመጠው የግዜ ገደብ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡<br>ምንጭ መልካም ተሞክሮ |

## አባሪ 3፡ በናሙና የተመረጡ መስሪያ ቤቶች ስም ዝርዝር

- የገቢዎች ሚኒስቴር
- የሰላም ሚኒስቴር
- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር
- የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን

አባሪ 4

ግዥ የሚፈጸምላቸው ተቋማት በ2015 በጀት አመት የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎችን ፍላጎት እንዲያቀርቡ 2 ጊዜ ተጠይቀው ለ3ኛ ጊዜ እንዲያቀርቡ መጠየቃቸውን የሚያሳይ የተቋማት ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | የመስሪ ቤት ስም | አድራሻ |
|---|---|---|
| 1 | መከላከያ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 2 | ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 3 | ቱሪዝም ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 4 | ማዕድን ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 5 | ግብርና ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 6 | ስራና ክህሎት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 7 | ፕላንና ልማት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 8 | ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 9 | ትምህርት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 10 | ኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 11 | ኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 12 | ኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 13 | አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 14 | ዕርቀ ሰላም ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 15 | ኢትዮጵያ ሃገራዊ ምክክር ኮሚሽን ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 16 | ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 17 | መንግስት ግዥ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 18 | ኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 19 | ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት | አዲስ አበባ |

| | | |
|---|---|---|
| 20 | ስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 21 | ኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 22 | ውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 23 | እንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 24 | አርቲፊሻል እንተለጀንስ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 25 | ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 26 | ኢትዮጵ ስፖርት አካዳሚ | አዲስ አበባ |
| 27 | ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 28 | ኢትዮጵያ ብሄራዊ ቲያትር | አዲስ አበባ |
| 29 | ኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ | አዲስ አበባ |
| 30 | ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 31 | ታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 32 | ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ | አዲስ አበባ |
| 33 | ለመንገድ ደህንነት መድን ፈንድ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 34 | ኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት | አዲስ አበባ |
| 35 | ኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 36 | ኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስትቲዩት | አዲስ አበባ |
| 37 | አርማወር ሀንስን ምርምር ኢንስትቲዩት | አዲስ አበባ |
| 38 | አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | አዲስ አበባ |
| 39 | ኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ | አዲስ አበባ |
| 40 | ኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 41 | ኢትዮጵያ ጅኦሎጂካል ኢንስትቲዩት | አዲስ አበባ |
| 42 | ማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት | አዲስ አበባ |

| | | |
|---|---|---|
| 43 | ኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| 44 | ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 45 | አርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ | አርዳይታ |
| 46 | አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 47 | ኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 48 | ገፈርሳ አዕምሮ ህሙማን ማገገሚያ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 49 | አቤት ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| 50 | ኢትዮጵያ ደን ልማት | አዲስ አበባ |
| 51 | አላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ | አዲስ አበባ |
| 52 | ኢትዮጵያ ህብረት ስራ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 53 | ኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 54 | ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 55 | አጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ | አርጋፋ |
| 56 | ገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ | ገዋኔ |
| 57 | ሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ | ሚዛን |